ይድረስ ለወጣቱ

አንተ ወጣት

ዛሬ እንዲህ ተዋርዳ ፤ የልማትና የሥልጣኔ ጭራ ሆና ያገኘሀት አገርህ ትላንት በዚህ በኔ (አንበሳ) አምሳል የምትታወቅ የተከበረች የነጻነትና የሥልጣኔ ግዙፍ ታሪክ የነበራት በተለይም ለአፍሪካና ለመላው ጥቁር ሕዝብ የነጻነት አርአያ ነበረች ።

በነጻነትና በሥልጣኔ ቀደምት በልማትም የዳቦ ቅርጫት የተባለች አገርህን የአንድነቷና የክብሯ አርማ የሆነውን ታሪካዊ ቅርስ አስወግዶ ደርግ የተሰኙ ወታደራዊ ጥርቅም ከማትወጣው የኢኮኖሚ አዘቅት ውስጥ መጣሉን እኔ ላንተ አልነግርህም ።

ያም ሳያንስ ቅድመ አያቶችህ ፤ አባቶችህ ፤ ታላላቅ ወንድሞችህና እህቶችህ በብልጽግናና በተድላ በኖሩባት ውድ አገርህ አንተ የሥራ እጦት ሰለባ ፤ የቁራሽ እንጀራ ቀላዋጭ ፤ ያም አልበቃ ብሎ እንደ ጦስ ዶሮ በየጎዳናው ተጠምዝዘህ እንድትወድቅና በእብሪት ያለፈቃድህ ከእናት ከአባትህ ጉያ ተነጥቀህ ለዱር አራዊትና ለአሞራ ምግብ አደረገህ ።

ያን ገናናና ታላቅ የእናት አገርህን ፖለቲካ ፤ ኢኮኖሚ ፤ ማህበራዊ ኑሮ ፤ ታሪክና ባህልህን እንዳል ነበር አዋርደው ። አሁንስ ምን ይመስልሃል? አባቶችህ በብዙ ተጋድሎና መስዋዕትነት ስላቆዩልህ ታሪክህስ ምን ታስባለህ ? አንድነትህ ፤ ነጻነትህ ፤ አኩሪ ታሪክህ ፤ ቅርስህ ጨዋነት የተመላውና የተላበሰው ልዩው ኢትዮጵያዊ ባህልህ ሲያያዝ በመጣው ሥርወ መንግሥት ለዘመናት የዞረ ድምር ውጤት መሆኑን ከታሪክና ከራስህ በላይ ሌላ አስረጂ ትፈልጋለህ ?

እንደ ዓለት ከጠጠረ የታሪክ እውነታስ የተሻለ ምን ማስረጃ ሊቀርብልህ ይችላል ?

ልብ በል

አገርህ ኢትዮጵያ ከፍጥረት መጀመሪያ አንስቶ በአምላኳ የታወቀች ፤ ስሟ በግልፅ በቅዱሳት መጻህፍት በመጽሐፍ ቅዱስ ከዘፍጥረት ምዕራፍ ፪ ቁጥር ፲፫ ጀምሮ ከ፵ ጊዜ በላይ የተጠቀሰች በቁርዓንም ነብዩ ሙሐመድ ተከታዮቻቸውን “ኢትዮጵያን አትውጉ ፤ ኢትዮጵያ የደጋግ ሕዝቦች አገር ናት ።” በማለት የተናገሩላትና የእስልምና እምነት ተከታዮችም በጦርነት ጊዜ ተሰደው የመጡባትና እንዲሁም ያለጦርነት የእስልምናና የክርስትና ሃይማኖትን የተቀበለች የእግዚአብሔር ሀገር ናት ።

የመጀመሪያዎቹ የሰው ዘሮች ኑሮ የጀመሩባት የነድቅነሽ (በፈረንጆቹ የሉሲ) ቅሪተ አፅም የተገኘባት አምሳለ ኤደን ገነት የሆነችና ዛሬም ቢሆን ለጤና ተስማሚ የሆነ ውብ አየሯ ፤ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥዋ ፤ የታሪክና የባህል ቅርስዋ የዓለምን ሕብረተሰብ ልብ የሚያማልል አገር ናት ።

ሕዝቦቿም ባለ አንድ ወጥ መልክ ፤ ቋንቋና ባሕል ሳይሆኑ እንደ አበባ ልዩልዩ (ቀይ ፤ ጥቁር ፤ ጠይም የቀይ ዳማ) መልክና እንዲሁም የልዩልዩ ቋንቋና ባህል ባለጸጎች ሲሆኑ ታሪካቸው ግን አንድ ነው ። አበሻ የሚለው ቃልም ይህኑን ስብጥር የሚያመለክት ነው ። ይህን የታደለ ከኢትዮጵያ ሌላ ማን አለ ? ነጩ ህዝብ መልኩ ነጭ ብቻ ነው ። ቋንቋውም ባህሉም አንድ ብቻ ጥቁሩም ቢጫውም ሕዝብ እንደዛው ።

ኢትዮጵያ ግን በ፲፱፻፷፩ ዓ-ም- በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ፴፰ኛው ዘመነ መንግሥት በአማርኛ በታተመው ቅዱስ ቁርዓን መግቢያ ላይ እንደተፃፈውና በተግባርም እንደሚታየው ፡-

«የኢትዮጵያ ሕዝብ በመልክ ፤ በታሪክ ፤ በዘርግንድ አንድ ከመሆኑም በላይ በአንድ ዘውድ ሥር የሚተዳደር በአንድ ህገ መንግሥት ያለውን የእኩልነት መብቱን የሚካፈል ስለሆነ ፤ ምንም በሀይማኖት የተለያየ እምነት ቢኖረውም በማህበራዊና በብሄራዊ ጉዳይ አንድነቱንና ወንድማማችነቱን አጥብቆ በመቆየቱ የኖረው ዝናውና የቆየው ታሪኩ ያቀዳጀው ክብሩና ገናናው ስሙ በዓለም ላይ አድናቆቱን ሳያጎድልበት ይኖራል ። ተከታዮቹን አንቀጾች በግልህ ብታነባቸው ለግንዛቤህ መዳበር ይረዱሀል ።

ቅዱስ ቁርዓን ፲፱፻፷፩ ዓ- ም-

በሌላም በኩል የሁሉም ዜጎች አገር መሆኗን ሲያመለክት “ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዥንጉርጉርቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን? በማለት የኢትዮጵያዊያን መልክ የተዥጎረጎረ ቢሆንም ዞሮ ዞሮ እንደ ነብሩ አንድ ፍጥረት መሆናቸውን ያመለክታል ። መ/ ቅዱስ በትንቢተ ኤርምያስ ምዕራፍ ፲፫ ቁጥር ፳፫ ጠላቶችዋ ግን ይህን የታሪክ እውነት ለመፃረር ሲሉ ስሟን ከቅዱሳት መፃሕፍት ላይ በማስፋቅ ይገኛሉ ይሁን እንጂ አምላኳ ከስዋ ጋር ስለሆነ በሳሉት ሰይፍ ራሳቸውን እየቀሉ ለመሆናቸው አንተም የቅርብ ምስክር ነህ ።

ልዩ ሕዝብ መሆንህንም አትዘንጋ ፤ ቢርብህም ቢጠማህም ከግንባርህ (ከፊትህ) የማይጠፋው ወዝህ ራሱ ሌላው ሕዝብ በአምባሬጭቃ ኀይል የሚያወዛው ላንተ ግን የተፈጥሮ ፀጋህ (መለያህ) ነው ።

አመጋገብህ ይሆን ለዚህ ምክንያቱ ? አዎ ምግብህም ፤ ከሌላው አለም ሕዝብ የተለየ ነው ። ባለጤፍ ባለእንሰት አገርና ተመጋቢ አንተው ኢትዮጵያዊ ሰው ነህ ። የሚወዛ እንጂ እንደሌሎች የሚያፈከፍክ ቆዳ የለህም ። የራስህ እንጂ የባእድ የባህል ተፅዕኖ የለብህም ፤ በአባቶችህ ተጋድሎ ለቅኝ ገዢዎች የተንበረከከ ጉልበት የለህምና ። የራስህ የሆነ ወጥ የአለባበስ፤ የአመጋገብ ባህል ያለህ ልዩ ሕዝብ ነህ ።

ብዙ አላበዛብህም ግን ማወቅ የሚገባህን የታሪክ እውነታዎችም ሳትረዳ ቀርተህ እንዳትወናበድና ለሥልጣን ጥመኞች የፍላጎት ማሟያ እንድትሆን አልፈልግምና የታሪክ ቀደምት ፤ የሥልጣኔ አምድ እንደነበርክም እስቲ ምሁራንን ጠይቅ ፤ ከአባቶችህ ተረዳ ፤ የታሪክ መፃሕፍትንም መርምር ።

ለመሆኑ ዛሬ የልማትና የስልጣኔ አንጋፋ ተብለው የሚደነቁልህ አገሮች ትላንት ካንተ የተሻሉ ሕዝቦች ነበሩ? ካንተስ የቀደመ ስልጣኔና ልማት ነበራቸው ? ዛሬስ ቢሆን በአግባቡ ተጠቅመህ ለብልጽግናና ለልማት ካዋልከው ካንተ የተሻለ ምን አላቸው ?

ሌላው ቀርቶ ፊደልህን ልብ ብለህ አይተኸዋል? የላቲን ፊደሎች እንኳ ያንተ ፊደል ቅጂ ለመሆናቸው የታሪክ መረጃ ትሻለህ? ለናሙና ያህል የሚከተሉትን ተመልከት ።

የላቲን ፊደል	የተወሰደው ከ	ጥንታዊ አፃፃፍ	ዘመናዊ አፃፃፍ
A	በ	ᗅ	*A*
B	መ	e	*B*
C	ር	C	*C*
D	ጋ	D	*D*
E	ሠ	ε	*E*

፳፮ቱም በዚህ ሁኔታ ይቀጥላሉ ። እነዚህም ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፬ሺ ፭፻ ዓ. ዓ. የነበሩ ፊደላት ናቸው ። ፊደልህም ሳያኮላትፍ ፤ ሳያጣምም ፤ የቋንቋውን ቃና ሳይለውጥ ማለት የተፈለገውን ድምጽ ማውጣት የሚችል በዓለም ካሉ ቋንቋዎች ሁሉ ልዩና የሰው ልጆች የመጀመሪያው ቋንቋ መሆኑ ይታመናል ፤ ታሪክም ያስገነዝባል ።

ጥቂቶች ግን ታሪክን ሳይመረምሩ የቅጂውን ቅጂ በመገልበጥ የተሻለ ያገኙ መስሏቸው ሲባዝኑ ይታያሉ ። የሚያሳዝን ነው ። የታሪክ እውነታው ግን ይኸው ነው ።

እንግዲህ ወዳጄ አስተውለው ይህ የታሪክና የሥልጣኔ ብኩርናቸው ለዘለቄታው እንዲቀጥል ለማድረግና በስውርም ሆነ በግልፅ አገርህን ከወራሪ ጠላትና ቅኝ ገዢ ለማዳን እንደ አፄ ቴዎድሮስ ያሉት የዚህችን በሁሉ ረገድ ልዩ ታሪክ ልዩ ውበት ፤ ልዩ ሥልጣኔና የተፈጥሮ ሀብት ባለፀጋ አገር ውርደት ከማየት በራሳቸው ፈረዱ ። ከነሱም ወዲህ የነበሩት ነገሥታት ለአንድነታቸውና ለነፃነታቸው ያደረጉትን ገድል ከታሪክ ማህደር ታገኘዋለህ ።

እስካሁን የነገርኩህ ሁሉ እውነተኛ ታሪክህ እንጂ ስብከት አይደለም ። ይኸ ሁሉ በዓለም ላይ እጅግ የሚያስደንቅህ አባቶችህ ያቆዩልህ ቅርስና ፤ ታሪክ ፤ ወራሽ አንተው ነህ ። ዛሬ የታሪክ ባላደራና ሃላፊም አንተው ነህ ። መልክህም ቋንቋህም ደምህም ኢትዮጵያዊ ነው ። ልዩ ታሪክ ፣ ልዩ መልክ ፤ ድፍርስ (አተላ) ደም ሊኖርህ አችልም ።

አባቶችህ አምነውብኝ የክብራቸውና የኩራታቸው አርማ አድርገውኝ፤ በመኖራቸው ከአንበሳ ያየለ ከዝሆን የገዘፈ ባለታሪክ ሆነው መቆየታቸውን አትዘንጋ ። የአራዊት ሁሉ ንጉሥ ነኝና ።

ኢትዮጵያህንና አባቶችህን በሌሎች ፍጥረታት ብትወክል ታሪክና ትውልድ ይፋረድሃል በትክክልስ የሚወክሉህ ይመስልሃል? ገናናነትህስ አድናቆትህስ የሚቀጥል ይመስልሃል? ።

ለእነዚህ ሁሉ ልዩና አኩሪ ቅርሶችህ መከበርና መዳበር አይነተኛ ሚና የተጫወተውን የአንድነትህንና የክብርህን አርማ ከሌሎች ቅርሶችህ ሁላ በክብርና በእንክብካቤ በሐላፊነት ማቆየቱ በማህበራዊም ሆነ በቁሳዊ ህይወትህ ለምትሻው ልማትና እድገት የሚኖረው አንጋፋ ድርሻ ከታሪካዊ እሴትነቱ ነጥለህ የማታየው ጉዳይ ነው ።

ወዳጄ ልብ በል

በአጭሩ እውነት እንነጋገር ከተባለ ሞዓ አንበሳ በዓለም ህብረተሰብ ዘንድ ሲያስከብርህ ፤ ሲያስሞግህስ የኖረው አይነተኛ ቅርስህ ነው ። ቅርሶችን ሁሉ በእንክብካቤና በጥንቃቄ ማቆየት እንዳለብህ ሁሉ ልዩ መታወቂያህን መኩሪያህን እንደ ጃፓንና እንደ እንግሊዝ በአክብሮት ማቆየቱ ጥቅሙ ለታሪክ ብቻ ሳይሆን ለአንተና ለትውልድ ነው ።

የዘውድ ባላደራዎቹ በስደት አገር ሳይቀር ስርዓቱ ሳይጓደል ቅርስ ጠብቀው አቆይተውልሃል ።

ቅርስህን ተቀብለህ ለትውልድ ማስተላለፍ ታሪካዊ ኃላፊነቱ አሁንም ያንተ ነው ።

ሞዓ አንበሳ የሚመራውን የዓጼ አምሃ ሥላሴ ህገመ ንግሥታዊ ዘውድ መቀበል ታሪካዊ ኃላፊነትህ ብቻ ሳይሆን ለሰላምና ለኤኮኖሚያዊ ህይወትህ መሻሻል መተኪያ የሌለው ብቸኛ ዋስትና መሆኑን አትዘጋ ።

እስካሁን በቁምህ ተዳፍኖብህ ፤ ጨልሞብህ ለቆየው ህይወትህ የብሩ ተስፋ ጭላንጭል የሚፈነጥቅልህ ብቻ ሳይሆን በእውን የሚከሰትልህ ይህን የክብር አርማህን ተቀብለህ አገርህን ስታረጋጋና የዓለምን ህብረተሰብ ሥነልቦና ስትማርክ ብቻ ነው ።

ለራስህ ታሪክና ባህል የማይገድህ ከሆንክ ብልሁ የዓለም ህብረኀብረተሰብም በትዝብት ከሚያይህና ከሚያሽሚጥጥህ በስተቀር አያዝንልህም ።

ታሪክ ቅርስና ባሕል ክቡር ነው ። ባይሆንማ እንግሊዝና ጃፓን እንደ ልማታቸውና ሥልጣኔአቸው ቢሆን ኑሮ ሕገ ንግሥታዊ ዘውድ ባላስፈለጋቸው ነበር ፤ ግን የብልጽግናቸው ምንጩ ዘውድ በመሆኑ ነው ።

ዛሬም ቢሆን በዚህ አርማ የሚተዳደረው ዘውድ ተመልሶ የቀድሞ የክብር ስፍራውን ሲይዝ ብቻ ነው በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ካፒታሊስቶችና ኢንተርፕረነሮች ለኢንቨስትመንታቸው ዋስትና የሚያገኙት በኢትዮጵያ ከፍተኛ የልማት እርዳታና እገዛ የሚያደርጉት የምዕራባውያን መንግሥታት ይኸንኑ በመጠባበቅ ይገኛሉ ።

ወዳጄ ሆይ አሁንም ለታሪክህ ለአገርህ አንድነት ሰላምና መረጋጋት ፤ ብሎም ለብልፅግናህና በዓለም ኀብረተሰብም ዘንድ ለሚኖርህ ተሰሚነት ዋስትናው እኔ ክቡር ምልክትህ ነኝና አስብበት ።

በዘመናዊው እንግሊዝና ጃፓን በሚመሩበት ህገ መንግሥታዊ ዘውድ አስተዳደር መመራት ለሁለንተናዊ ህይወትህ ደህንነት አማራጭ የሌለው ታሪካዊ ዋስትናህ በመሆኑ በማንም በምንም ሳትዘናጋና ሳትወናበድ እውነተኛና ትክክለኛውን ታሪክህንም ለትውልድ አስተላልፍ ።

ሞዓ አንበሳ